


እንኳን ለጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ የጥምቀት በዓል በሰላም አደረሳችሁ።

¾Ñ>¹²?¹²›ÖnkU_



የሥልጠና¨< ¯LT:-

- የግቢ ጉባኤ ›vLf ሰለ Ñ>²? ›ÖnkU በቂ ግንዛቤ ኖbቸዉ በዓለማዊ ትምህርታቸው አመርቂ ውጤት ከማምጣት በተጨማሪ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ጊዜ በመስጠት ቤተ ክርስቲያንን በተሰጣቸዉ ፀጋ እንዲያገለግሉ ማስቻል


Exam
study
lovers
Internals
parents
Student
Teachers
attendance
backlogs

ጊዜ ምንድን ነዉ?

- የተለየ፣የተወሰነ ሰዓት፣ዕለት፣ወርኀ፣ዓመት፣ዘመን፣ዕድሜ፣ሰዉ እስኪሞት የሚኖርበት የሚያርፍበት የሚሠራበት ሌሊትና መዓልት 24 ሰዓት ማለት ነዉ።
- ጊዜ ለሁላችን እኩል የታደለ ሀብት ነው። ቢሆንም ጠቀሜታው ግን ለሁላችን እኩል አይደለም።
- ስለዚህ ለጊዜ ጊዜ መስጠት በጣም አስፈላጊ ነው ማለት ነው።

- ጊዜ ማለት ራሱ ሰው ነው። (ጧት፣ቀን፣ማታ፣ሌሊት- ህፃንነት፣ ወጣትነ፣ ሽምግልና፣ ሞት)
- አንድን ፈላስፋ ዘመኑ እንዴት ነው አሉት? “ዘመን አንተ ራስህ ነህ።ስትለወጥ ይለወጣል፤ ስትከፋ ደግሞ ይከፋል።”
- ከእግዚአብሔር ስጦታዎች አንዱ ጊዜ ነው። በሰው እጅ ያለ ፣የማይለዋወጥ ለሁሉም በእኩል የተሰጠ ነው።
- ድኃ ባለጸጋ አያበላልጥም ለሁሉም እኩል ነው። ለጥቅም ወይም ለስራ የተሰጠም ነው።
- አንድ ሰው በኖረ ቁጥር ከዕድሜው ባንክ ነው የሚጠቀመው።
- ሰው በራሱ አካል (ዕድሜ) ነው የሚኖረው። አላግባብ እንዳይኖር ግን ጥንቃቄ ያስፈልጋል።

የጊዜ ጠባያት

1. ጊዜ ገለልተኛ ነው። (time is neutral)
2. ጊዜን ቆጥቦ ለወደፊት መጠቀም አይቻልም (time can’t be saved for future use)
3. ጊዜ እንደ ገንዘብ ዋጋ አለው **(time has value like currency)**
4. ጊዜ በጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ልዩነት ይፈጥራል።

1. ጊዜን ለጊዜ አጠቃቀም መስጠት፤

- ጧት ወይም ማታ እንዳመችነቱ አንድ ሰው አንድ ሰዓት በመመደብ የቀን፣ የሳምንት፣ የወርና የዓመት፣አጠቃላይ ሂደቶችን ጊዜ ሰጥቶ በማየት የተቀረጉት አዲስ ቀናት፣ ሳምንት፣ ወራትና ዓመት በተሳካ ሁኔታ ማስኬድ ይችላል።

60 ደቂቃውም በሚከተለው መልኩ ከፋፍሎ መጠቀም ያስፈልጋል።

1. 15 ደቂቃ- ያለፈው ጊዜ ደካማና ጠንካራ ጎን መለስ ብለን የምንቃኝበት ነው።በዚህም ድክምታችንና ጥንካሬያችን ለይተን መማፍ ይኖርብናል።
2. 15 ደቂቃ- ራዕያችንን ያሉብንን ኃላፊነቶች የምንቃኝበትና የምንጽፍበት ጊዜ ነው።
3. 15 ደቂቃ- ከራዕያችንና ካሉብን ኃላፊነቶች በመነሳት ለቀጣዩ ቀን ፣ ሳምንት ወርና ዓመት የምንሰራውን በቅደም ተከተል የምንጽፍበት ጊዜ ነው።
4. 15 ደቂቃ- ፈጣሪያችን እግዚአብሔር አምላክ የምናመሰግንበትና የምንፈልገውን እንድናገኝ የሚረዳን ማስተዋልን ጥበብን የምንጠይቅበት ጊዜ ነው።

2. ግብ ማስቀመጥ (setting goals):-

- ማንኛውም ሰው ላለበት ኃላፊነቶች ግብ ማስቀመጥ ይኖርበታል። ለዚህም ነው “ውጤታማ ለመሆን ካላቀድክ ለመውደቅ አቅደሃል” የሚባለው

3. ቅደም ተከተል ማውጣት (setting priorities):-

- ቅደም ተከተል ማስያዝ ካልቻልን የጊዜ እጥረት በሚያጋጥምበት ወቅት በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ትተን ብዙ ትርጉም በማይሰጡ ጉዳዮች ጊዜያችን ልናጠፋ እንችላለን።

ቅደም ተከተል ለማስያዝ የምንጠቀመው መስፈርት፡-

ሀ. ከሐላፊነት አንጻር

- ግድ መሠራት ያለበት (Must to Do)--ማደር የማይችሉ
- መሠራት ያለበት (Should to Do) - የማደር ዕድል ያላቸው
- መሠራት የሚገባው (Ought to Do)- በሌላም መሰራት የሚችል ቢያድርም ችግር የሌለው

ለ. ከአስፈላጊነትና አስቸኳይነት አንፃር (Importance & Urgency)

- አስፈላጊና አስቸኳይ (Important & Urgent)
- አስፈላጊና አስቸኳይ ያልሆነ (Important & Non-Urgent)
- አላስፈላጊና አስቸኳይ (Non- Important & Urgent)
- አላስፈላጊና አስቸኳይ ያልሆነ (Non- Important & Non -

4. አእምሮአችን በተፈጥሮ ንቁ የሚሆንበትን ጊዜ መለየት (Identifying Your Biological Prime Time)_

5. ትክክለኛውን ነገር በትክክለኛው ጊዜ አሁኑኑ መሥራት (Do Right Things Right Now)

6. ሐላፊነትን ማካፈል (Practice Delegation)

- “We are not the only best person to do everything”

7. እንቢ ማለት ልመዱ **(Practice to Say “No”)**

- ይህም ሰዎች የእኛን በዕቅድና በጊዜ መመራት ቢዘገዩም ማድነቃቸው አይቀርምና ነው።
- ስለዚህም ከዕቅዳችን የሚያስወጡ ጉዳዮችን ወይም ግለሰቦች (“Dream Stealer’s”) እንቢ ማለቱን መልመድ ይኖርብናል።

8. ራስን መፈተሸና መሸለም **(Evalutate & Reward Yorself)**


- ራሳችን ወደዚህ ልምድ ለማምጣት የቀን ውሎ (Diary) የመፃፍ ልምድ ልናዳብር ያስፈልጋል።

የጊዜ አጠቃቀም ጥቅሞች (Benefits of Time Mgt)

- **በሌሎች ዘንድ የሚኖረን ተቀባይነት ከፍ ይላል (Respect by Others Will Increase)**
- **የተመጣጠነ ሕይወት እንድንመራ ያስችለናል (We Can Have a Balanced Life)** መንፈሳዊ፣ አዕምሮአዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ጤናዊ
- **ውጤታማነታችን (Increase Productivity)**
  - ጊዜያችን በአግባቡ የምንጠቀም ከሆነ በሁሉም ረገድ በትንሽ ጊዜ ብዙ ሥራዎችን በማከናወን ውጤታማ (Productive-Effective & Efficient) መሆን እንችላለን።




የንባብ ባሕል



"Reading is to the mind like running is to the body. If a person wants to exercise their mind, read a good book."
~Lamar Cole

- እውቀት መገኛው ብዙ ነው።
  - መደበኛ ትምህርት
  - የሕይወት ልምድ
  - መጠየቅ
  - ንባብ
- የሰው አእምሮ በተፈጥሮው እያደገ የሚሄድ ሲሆን የእድገቱ መጠን ግን በሰውየው ጥረት፣ በአካባቢው ተጽእኖ፣ በሌሎችም ሊወሰን ይችላል።

LANGUAGE SKILLS



Reading *IS* Thinking

"The purpose of reading is understanding."

- ማንበብ /ንባብ
  - ✓ ጽሑፍን ወይም ምስልን በገቢር የመረዳት ሂደት ነው።
  - ✓ የማሰብ ሂደት ነው።
  - ✓ ንባብ በዝምታ ውስጥ ያለ ጫጫታ ነው።
- ✓ ንባብ በዚህ ተለዋዋጭ በሆነው ዓለም ከአዳዲስ እውቀቶች ጋር ራስን እያለማመዱ ለመሄድ ይጠቅማል።
- ውጤታማ አንባቢዎች መቼና ምን እንደሚያነቡ ያውቃሉ
- በማንበብ ሂደትም ምን እንደሚያነቡ ራሳቸውን ይከታተላሉ

- ንባብ
  - እውቀት ይጨምራል
  - ነገሮችን ያቀላል
  - ችግር የመፍታት ዘዴን ያለማምዳል
  - የመናገር/የመጻፍ ችሎታን ያሳድጋል
  - አስተሳሰብን ያሰፋል
  - ከምንፈልገው ደረጃ ያደርሳል
  - መልስ አያሳጣም
  - ንባብ አፍ ያሰፋል።

- ማር ይስሐቅ “ሥጋ ራሱ በድን ነው፥ ነፍስ ቢጨመርለት ሕይወት ይኖረዋል። ነፍስ በራሷ ብቻዋን ስትሆን ደግሞ በድን ናት። ንባብና እውቀት ሲጨመርላት ሕይወት ያላት ትሆናለች አለ።”
- ጊዜን የተጠቀመ ማን ነው? ለምሳሌ ዮሐንስ አፈወርቅ **980** መጻሕፍትን ጻፈ። እንዴት ፃፈ? አንድ ሰው በህይወት ዘመኑ ጥናት ቢሰራ ስንት ጥናት ሊሰራ ይችላል?
- እግዚአብሔር በመዓልትም ሰርቷል በሌሊትም ሰርቷል።በሌሊት የፈጠራቸው ፍጥረታት አሉ፥ በመዓልትም ሰውን ፈጥሮበታል፥ ስለዚህ የመዓልትም የሌሊትም ባለቤት እግዚአብሔር በሁለቱም ሰርቶበታል። እኛንም እንደዚያ እንድንሰራ ተፈጥረናል።

የማያነብ ሰው

- እውቀቱ ውስን ነው
- የሚናገረው የለውም
- ሀሳቡን በአግባቡ መግለጽ አይችልም
- ቀላል ነገሮች ሁሉ ውስብስብ ይሆኑበታል
- የመፍትሔ ሰው አይደለም
- ሳያውቅ ያወቅሁ ይመስለዋል
- ጥቃቅን ችግሮችን እንኳን መፍታት አይችልም
- የተግባቦት ክህሎቱ ደካማ ነው
- ሥራ መፍጠር አይችልም
- የሚኖርበትን ዓለም አያውቅም
- ንግግሩ አሰልች ይሆናል
- በሥራው ሁሉ ውጤታማ አይሆንም
- በራስ መተማመን ይጎድለዋል

የንባብ ሰው

- የንባብ ሰው በሁሉም ቦታ ንጉሥ ነው።
- የንባብ ሰው ሁሉንም ማየት የሚችል ነው። ሲፈልግ ከጽርሐ አርያም በላይ ሲፈልግ ከጽርሐ አርያም በታች ሲፈልግ ከሰው ልቡና ውስጥ ይኖራል።
- መንፈሳዊውን ስታነብ የጳውሎስን ልብ ላይ ትኖራለህ። ዓለማዊውን ስታነብ በደራሲው ልብ ውስጥ ትኖራለህ።
- ባላነበብክ ቁጥር ትርቃለህ። ባነበብክ መጠን ትቀርባለህ።
- በንባብ ውስጥ ኑር “ወዘሕጎ ያነብብ መዓልተ ወሌሊተ ወይከውን ከመ ዕፅ እንተ ትክልት ኀበ ሙኀዘ ማይ...”

የንባብ ባሕል

- የንባብ ባሕል ስንል
  - ✓ የሰዎች ንባብን የመውደድ ጠባይ
  - ✓ የንባብ ዓይነቶች
  - ✓ የማንበብ ጣዕም ማለታችን ነው።
  - አንድ ግለሰብ ንባቡን የሚያደራጅበት ሁኔታ ነው።
- ማንበብ መቻል **በራስ የመማር** እና **የእድሜ ልክ ትምህርት** ማእከል ነው።
- ሆኖም ግን የአብዛኞቻችን የንባብ ልምድ አበረታች አይመስልም (በተለይ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች የምንገኝ ሕዝቦች)

ለምን አናነብም?

- እንቅልፍ
  - እንቅልፍ ልምምድ ነው። በሰጠህው መጠን ነው የሚሄደው።የማይተኛ እና ውኃ የማያበዘ ሰው ንጽህናውን ጠብቆ ይኖራል።
- አብዝቶ መብላትና አብዝቶ መጠጣት
- ፊልም (የሰው አድናቂ ሆኖ መቅረት)

- ኳስ
  - ሮናልዶ-
  - መሲ-
  - ሮናልዲኖ ጎቹ
- ማድሪድ
- ባርሳ
- ባየርሞኒክ

ከኳስ በፊት የወንበር መያዣ ሰዓት፤ ከኳስ በኋላ ያለው ጭቅጭቅ፣ድብድብ፣

- ማኅበራዊ ሚድያ
- ወሬ ማብዛት (Chat via telegram,FB)

ማኅበራዊ ሚድያ ተጠቃሚ በዓለም

- ከ4ቢሊዮን በላይ ኢንተርኔት ተጠቃሚ፤ ከእነዚህ ውስጥ የአንድ ቢሊዮን 1/4ኛ ለመጀመርያ ጊዜ በ2017 ብቻ ተጠቃሚ የሆኑ
- በአፍሪካ በየዓመቱ የኢንተርኔት ተጠቃሚው በ20% ይጨምራል።
- 2/3ኛ የዓለም ህዝብ (7.6ቢሊ) ሞባይል አለው።ከግማሽ በላይ ደግሞ ስማርት ስልክ ናቸው።
- በ2018 4.021 ቢሊዮን ኢንተርኔት ተጠቃሚ (የ7% ጭማሪ ከ 2017 ሲነጻጸር)
- በ2018 ሞባይል ተጠቃሚ ወደ 5.135 ቢሊዮን (የ4% ጭማሪ) ደርሷል።
- አንድ ሰው በአማካይ በቀን ለ6 ሰዓት ያህል ኢንተርኔት ይጠቀማል።ይህን በ4 ቢሊዮን ተጠቃሚ ብናበዛው 1 ቢልዮን ዓመት ኦንላይን
- በየቀኑ 11 አዲስ ሰዎች ኢንተርኔት መጠቀምን ይጀምራሉ።
- 2.5 ቢሊዮን FB ተጠቃሚ በዓለም
- የብርቲሽ ወጣቶች በቀን 188ደቂቃ ለኢንተርኔት ያጠፉሉ
- በአውሮፓ ተማሪዎች ጋ በተደረገ ጥናት ተማሪዎች በዓመት 12000 ሰዓት ለትምርት ሲያጠፉ 18000 ሰዓት ደግሞ ለሚድያ ያጠፉሉ።
- አገራችንስ ወይስ አፍሪካ? እኛስ?

የንባብ ባህል በኢትዮጵያ

- “ኢ/ያውን ከንባቡ ይልቅ ወደ ንግግሩ ያደላሉ።”
- “ገንዘብህ እንዳይሰረቅ ከፊለግክ መጽሐፍ ውስጥ አስቀምጠው”

በኢ/ያ ውስጥ፦

- በሳምንት የሚታተሙ ጋዜጦች ሁሉም ተደምረው 100,000 አይሞሉም
- ከመማርያ መጻሕፍት ውጪ የሚታተሙ በብዛ 10,000 ቅጅ ናቸው።
- በሳምንት ውስጥ የሚታተሙ መጽሔቶች በብዛ 30,000 ቢሆኑ ነው።

- ከምዕራባውያን ጋር አንድ ባቡር ውስጥ የመሳፈር እድል ቢኖር ምንም ዓይነት የሚረብሽ ድምፅ አይሰማም።
- አፍሪካ ሃገር (ኬንያ፣ ዑጋንዳ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ሌሴቶን) 4/10 ያነባሉ።
- ኬንያ ጉልት ሻጭ ሳይቀር የሚነበብ ጋዜጣ ይይዛሉ።

ታዲያ የንባብ ባህላችንን እንዴት እናሳድግ?

የንባብ ዓይነቶች

1. የሚለማ ንባብ (Scanning)-

- ሁሉንም ጽሑፍ ሳናነብ የምንፈልገውን የመረጃ ክፍል ብቻ ለማግኘት መሞከር
  - ውስን መረጃ ለማግኘት በፍጥነት ከመረጃው ጋር ተያያዥ የሆኑ ቃላት ወይም ሀረጋትን መፈለግ
  - አንባቢው የጽሑፉን አካል በሰፊ እይታና በፍጥነት ማየትን ይጠይቃል።

2. ግርድፍ ንባብ (Skimming)፡

- አንድን ጽሑፍ ቃል በቃል ሳያነቡ የጽሑፉን ሙሉ ሀሳብ ለመረዳት መሞከር
- የመጀመሪያና የመጨረሻ አንቀጾችን፣ ርእሶችንና ንዑሳን ርእሶችን፣ ደመቅ ብለው የሚታዩትን/ለየት ብለው የተጻፉትን፣ ምስሎችንና መግለጫዎችን ብቻ በማየት የጽሑፉን ዋናውን ጭብጥ ለማግኘት መሞከር ነው።

3. ቀላል ንባብ (Light reading)

- በአብዛኛው ለመዝናናት ስናነብ:
  - አንባቢው ምኞት በሚሰጠው መልኩ ሲያነብ
  - እየተገነዘበ ሲያነብ
  - አሰልቺና ጠቃሚ ያልሆነውን እያለፈ
- በአማካይ ከ100-200 ቃላት በደቂቃ
- የዚህ ዕይነት ንባብ ጥልቅ ተመስጦን አይጠይቅም

4. የቃል በቃል ንባብ (Word by word reading)

- ብዙ ጊዜና ከፍተኛ ተመስጦ ይጠይቃል
- በአብዛኛው ከዚህ በፊት የማናውቀውን ጽንሰ ሀሳብ ወይም ሳይንሳዊ ትንታኔዎችን ለማወቅ

5. ለማጥናት ማንበብ (Reading to study)

- አንድን ጽሑፍ በጥልቀት ለመረዳት የሚደረግ ንባብ ነው።
- አምስት ደረጃዎች አሉት
  - ዳሰሳ (Survey)፡ ቁልፉን ሀሳብ ሳይሆን ስለ ጽሑፉ አጠቃላይ ሁኔታ ለማግኘት
  - ጥያቄ (Question)፡ ጽሑፉ እንዲመልሰው የምንፈልገውን ጥያቄ ማንሳት
  - ማንበብ (Read): በዝግታና በጥንቃቄ
  - ማስታወስ (Recall): ያነበብነውን እያስታወስን ዋናውን ሀሳብ ለመጻፍ መሞከር
  - ዞሮ ማየት (Review): ጥያቄዎቻችንን ዞሮ በማየት አስታውሰን ከጻፍነው ጋር ማነጻጸር እንዲሁም ጽሁፉ ጥያቄዎችን ምን ያህል እንደመለሰልን ማየት፣ ክፍተት ካለ እንደገና ማንበብና ማስታወሻ መያዝ

የግል ውይይት

- መጻሕፍትን የመግዛት ልምዳችን ምን ይመስላል?
- የማንበብ ልምዳችንስ?
- እንዳናነብ የሚያደርጉን ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
- የማንበብ ባሕላችንን እንዴት ማዳበር ይቻላል?

የንባብ ባሕልን ለማሳደግ ጠቃሚ ምክሮች

1. **ጊዜ መስጠት፡** አንድ ሰው በየቀኑ ሳያነብ መዋል/ማደር የለበትም።
   - የሚያነበው ነገር ምንም ይሁን ጥቂት ጊዜ ሰጥቶ ማንበብ አስፈላጊ ነው።
   - ለምሳሌ፡ ምንም በሥራ ብንወጣጠርም ቁርስ ከበላን በኋላ ለ10 ደቂቃ፣ ምሳ 10 ደቂቃ፣ ራት 10 ደቂቃ፣ ስንተኛ 10 ደቂቃ ብናነብ በቀን 40 ደቂቃ ማንበብ እንችላለን ማለት ነው።
   - በእርግጥ ብዙዎቻችን ያለሥራ የምናባክነው ጊዜያችን ሥፍር ቁጥር የለውም
     - በመዝናናት፣ በማውራት፣ ካፊ በመቀመጥ፣ኳስ፣ሃሜት ....

- በሳምንቱ ውስጥ የንባብ ቀን ወይም በቀን የንባብ ሰዓት መወሰን እና በዚያ ቀን ወይም ሰዓት ሌላ ሥራ አለመሥራት

"No matter how busy you may think you are,
you must find time for reading,
or surrender yourself to self-chosen ignorance."
~Atwood H. Townsend



2. ሁልጊዜ መጻሕፍት ይዞ መንቀሳቀስ፡

- የትም ስንሄድ መጽሐፍ ከእኛ ጋር ሊኖር ይገባል
- ባገኘነው ክፍተት ሁሉ እንድናነብ ይረዳናል

3. ማንበብ የምንፈልጋቸውን መጻሕፍት ዝርዝር ማዘጋጀት

- በተለያዩ ምክንያቶች እንድናነብ የተጋበዝናቸው ወይም ጥሩ መጻሕፍት እንደሆኑ የተነገሩን ካሉ

4. ጸጥ ያለና ለንባብ ምቹ ቦታ መምረጥ

- ወንበር፣ ጠረጴዛ በማዘጋጀት አካባቢያችንን ለንባብ ዝግጁ ማድረግ
- ለመተኛት ካልሆነ በስተቀር ፍራሽ ላይ ለማንበብ መቀመጥ የለብንም
- ማንኛውም ሊረብሽ የሚችል ድምጽን ማጥፋት (TV, Radio, children...)

5. የሚዲያ አጠቃቀማችንን ማስተካከል

ቴሌቪዥን፣ ኢንተርኔት (FB,Linkedin,twitter...) መቀነስ የንባብ ጊዜያችንን ይጨምርልናል

6. ለልጆቻችን/ለጓደኞቻችን ማንበብ

- ሌሎች የንባብ ፍቅር እንዲኖራቸው ያደርጋል
- የራሳችንን የንባብ ባሕል ማዳበር እንችላለን

7. ስለነበብናቸው መጻሕፍት ማስታወሻ ማስቀመጥ

- ስለ መጽሐፉ የራሳችንን አስተያየት ሊሆን ይችላል

8. መጻሕፍትን መግዛት

- ምግብ የሌለው ሰው ሊበላ አይችልም
- የሌለንን ልናነብ አንችልም
- መጻሕፍትን መግዛት ባሕል ልናደርግ ይገባናል።

9. ወደ ቤተ መጻሕፍት መሄድን ልማድ ማድረግ

- ቢያንስ በሳምንት አንድ ቀን
- በቤታችንም ትንሽ ቤተ መጻሕፍት (Mini Library) ቢኖረን

10. የንባብ ልምዳችን እስከሚያድግ አዝናኝና ቀለል ያሉ መጻሕፍትን ማንበብ

- ልብወለድ፣ ታሪክ፣ ...
- ቀስ በቀስ ወደ ከባድ ጽንሰ ሀሳቦች ማደግ

11. የንባብን ጊዜ አስደሳች ማድረግ

- የቀኑ ምርጥ ጊዜ እንዲሆን ማድረግ
- መናፈሻ አካባቢ፣ ጂት፣ ማታ ...

12. ትልቅ የሚያሳይ ግብ ማስቀመጥ

- በቀን 3 ሰዓት አነባለሁ።
- በዓመት 50 መጻሕፍት አነባለሁ ...

13. ይዘትን መሠረት ያደረገ አነባበብ መልመድ

- አንድን መጽሐፍ አንብበን ከጨረስን በጎላ ያነበብነውን ለማስታወስ ስንሞክር ምንም ትዝ ላይለን ይችላል።
- አንድ ርእሰ ጉዳይ በመምረጥ በዚያ ዙሪያ ብዙ መጻሕፍትን ማገላበጥ ጠቃሚ ነው።
- ይህም ማስታወሻ ከመያዝ ጋር ሊሆን ይገባል።

14. በቡድን ማንበብ

- ከ4-8 የሚሆኑ ሰዎች በአንድ ላይ በመሆን የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮችን በመከፋፈል በዚያ ዙሪያ ያሉ ዕውቀቶችን አንብቦ በመምጣት ለሌላው ማካፈል።
- በውይይት ቢታገዝ የበለጠ ውጤታማ ይሆናል።

15. የንባብ ክህሎትን ማዳበር

- የማንበብ ችሎታችን የማንበብ ፍላጎታችንን ይወስነዋል

5 MB hard drive in 1956



128 GB pen drive in 2017



በራሳችን የምንመልሳቸው ጥያቄዎች፦


- ለመሆኑ በሳምንት ውስጥ ለሻሂ፣ ለቡናና ለማኪያቶ ከምናወጣውና ለመጻህፍት ለመጽሔቶች ወይም ለጋዜጦች መግዣ ከምናወጣው የቱ ይበልጣል?
- አንድ ሰው 30 ዓመት እስኪሞላው 30 መጻሕፍት አንብቦ ይሆን?
- በቤታችን ከብርጭቆው (ከሲኒው) ከመጻሕፍት የትኛው ይበልጣል?
- ስንቶቻችንስ ከተማርንባቸው መጻህፍት ውጭ አንብበናል?
- ለሞባይል ካርድና ለመጻሕፍት መግዣ የምናወጣውን ስናመዛዝነው የቱ ይበልጣል?
- ለወሬና ለንባብ ከምናወጣው ጊዜስ የቱ ያመዝናል?
- ሰማሁ ብሎ ከሚናገረውና አነበብኩ ብሎ ከሚናገረው የቱ ይበዛል?
- ለምን የመጻሕፍት መሸጫ ቤቶችና የጫት ቤቶች አይመጣጠኑም?
- ለልጅ ከረሜላና ጀላቲ ነው እንጂ መጽሐፍ ተገዝቶ አይሰጠውም?

ማኅበረ ቅዱሳን ለእኛ ያዘጋጃቸው፦

- ጉባኤ ቃና
  - ለግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች የምትዘጋጅና በየ ሁለት ወሩ የምትወጣ መጽሔት ናት።
  - በሁለት ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛና በኦሮምኛ
- ስምዓ ጽድቅ - በየሁለት ሳምንቱ
- ሐመር - በየወሩ
- የተለያዩ መጻሕፍቶች
- Website:- gibi.eotcmk.org

ጠቃሚ ዌብሳይቶች

- ይህን መጽሐፍ ብላ ህዝ ጅ ተመልከት/ http://eathebook.org
- www.eotcmk.org
- www.ethiopianorthodox.org
- debelo.org/home


Sense
Check Understanding
Build Fluency
Reading skills
Connect To Text
Ask Questions
Decide What's Important
Making Inferences/ Draw Conclusions
Expand Vocabulary
Predict and Prove
Summarize/ Synthesize

“Today a reader, tomorrow a leader.”

~Margaret Fuller

ወስብሐት
ለእግዚአብሔር